# ፍየል ወዲህ...

## ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

በሽር አህመድ 11-26-14

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉባቸው፣ በአገሪቱ ያለውን የድህነት ሁኔታ ለመቅረፍ የጎላ ፋይዳ ያላቸው የልማት ተግባራት ናቸው - እነዚህ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች፡፡ እነዚህን ማጣጣልና የልማቱ ተሳታፊ የሆኑ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ተሳትፎ ለማቀዝቀዝ ያለሙ ተግባራትን በመፈፀም ላይ ይገኛሉ -ተቃዋሚዎቹ።

በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ያሉት ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶችን ለማሳካት የሚደረገውን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍ የሕዝብ ተሳትፎ ለማቀዝቀዝና ህዝቡ የራሱን ልማትና ብልፅግና የአገሩን ዕድገት እንዲቃወም ያስችላል ያለውን ስትራቴጂ ነድፎ በመተግበር ላይ ነው - በተለይ ሰማያዊ ፓርቲ።

የፓርቲው የእስካሁን ጉዞና ተግባር እንደሚያሳየው ለሕዝብ የሚጠቅም አጀንዳ ያልያዘ መሆኑን ነው። ይህ ነው የሚባል በኢትዮጵያ ፖለቲካ የጎላ ሚና ያለው ተሳትፎ ሲያደርግም አልታየም። ይልቁን በአገሪቱ ወቅታዊ የሆኑ ችግር መስለው የታዩትን አጀንዳዎች እየመዘዘ የማባባስ ተግባርን እያደረገ ይገኛል። የአገሪቱን የሕግ ሥርዓት የማደፍረስ፣ በየጊዜው ዓላማውንና ሃሳቡን በመቀያየር ወቅታዊ ሁነቶችን እየተከተለና ብሶት አለባቸው ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን እያሰባሰበ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚጣረሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ተደናግሮ ሌሎችን እያደናገረ ያለ ፓርቲ ነው።

የአገሪቱን ሕግ ተላልፈውና ወንጀል ፈጽመው ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ማረሚያ ቤት የገቡ ግለሰቦች ዘመዶችን በማሰባሰብ እየተንቀሳቀሰ ያለው ይህ

የፖለቲካ ድርጅት ለህዝብ የማይጠቅም ዓላማ መያዙ  ተግባራዊ  እንቅስቃሴው ህያው ምስክር ነው።

መስከረም 12 ቀን 2006 ዓ.ም ፓርቲው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ባቀረበው ጥያቄ  መሠረት መንግሥት በሕገ መንግሥቱ መሠረት ፈቃድ ሰጠው። ፓርቲው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፉን እንዲያደርግ የተፈቀደለት በጃንሜዳ ነበር። ለዚህ ደግሞ መንግሥት በወቅቱ በቂ ማብራሪያ ሰጥቶበት ነበር። መስቀል አደባባይ በመባል የሚታወቀው አካባቢ የባቡር መንገድ ግንባታ ላይ በመሆኑ ምክንያት የትራፊክ መጨናነቅና መዘጋትን ስለሚያስከትልና ይህ ደግሞ በተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል ላይ ጫና ስለሚያሳድር የሚል ነበር።

ፓርቲው ግን ባልተለመደ መልኩ የተሰጠውን ፈቃድ በመተው በመስቀል አደባባይ መሰለፍ አለብኝ በሚል በተለያዩ የማኅበረሰብ ሚዲያዎች ሰፊ ዘመቻና መንግሥትን የማጥላላት እንቅስቃሴ ማድረግን መርጦ ነበር።  ሰላማዊ ሰልፌን በመስቀል አደባባይ እንጂ  በጃንሜዳ መካሄድ  የለበትም በሚል ተገቢ ያልሆነ አተካራ ውስጥ   ገብቶ እንደነበርና   ባልተፈቀደለት ቦታ ሰላማዊ ሰልፉን ለማድረግና  በአዲስ አበባ ከተማ ሁከት  ለመፍጠር  ጥረት ማድረጉም ይታወቃል ።

መንግሥት በአገራቱ እየጎለበተ የመጣው የዴሞክራሲ ሥርዓት  የበለጠ ለማጠናከርና የሕዝቡን የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት እንዳይሸራረፍ ለማድረግ እያደረገ ባለው  ጥረት  ምክንያት በርካታ  የህግ ጥሰቶችን  መታገስን መርጦ እየሰራ ይገኛል። ይህ ግን በህዝቡ ዘንድ ጥያቄ እያስነሳ ይገኛል። በህዝብ ላይ ያነጣጠረ የሁከትና የጥፋት እንቅስቃሴ መገታት እንዳለበትም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከመግለጽ አልተቆጠበም።  ፓርቲው በምን ተግዴ የአገሪቱን ሕገ መንግሥት በጣሰ መንገድ ሕዝብን የማተራመስና የማወክ መርዙን በመርጨት ላይ  መሆኑን ከተግባሩ ለመረዳት  ይቻላል።

ፓርቲው የተቃውሞ ሠልፍ ለማድረግ ቦታ የተከለከለ በማስመሰል ውዝግብር ሲነዛ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ፕሮፖጋንዳ የዓለምን ህዝብ ትኩረት ለመሳብ ጭምር አልሞ በተለያዩ ሚዲያዎች አስተጋብቶታል።

መንግሥት በበኩሉ ለፓርቲዎች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው የሆነውን የተቃውሞ ሰልፍ ፍቃድ በመሥጠትና ቦታውን ለይቶ የማሳወቅ ግዴታውን እየተወጣ ይገኛል። ነገር ግን እንደ ሰማያዊ ፓርቲ ያሉት የተቃዋሚ ፓርቲዎች የተፈቀደው ቦታ የትም ይሁን የት ምንም ሳያቅማሙ ደንቡን በመተላለፍ በጉልበት ወደፈለጉበት ቦታ ሰልፉን ለማካሄድ ሲውተረተሩ ታይተዋል።

በቅርቡ በአፍሪካ እየተጠናከረ የመጣውን የአክራሪነትና የፅንፈኝነትን እንቅስቃሴ እንደ ትልቅ የፖለቲካ አጋጣሚ አድርጎ እየተጠቀመ ያለው ይህ ፓርቲ በተለይ የዋሃቢ ሰለፍያ አክራሪ ቡድንን የፓርቲው የፖለቲካ ማራመጃ መሣሪያ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በሽብር ድርጊታቸው የህግ እስረኛ ለሆኑት ግለሰቦች ዋስ ጠበቃ የሆነ መስሎ መቅረብም ዋና ተግባሩ አድርጎታል። ፓርቲው በሕገ መንግሥቱ የተጎናፀፈውን መብት መልሶ ራሱ በመካድ አማራጭ ሕገ መንግሥት አርቅቄያለሁ በሚል አንድ ሰሞን የፕሮፖጋንዳ ሥራ ማከናወኑ ይታወቃል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ፓርቲው ለሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ታማኝ አለመሆኑና በሕገ መንግሥቱ ማዕቀፍ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ አለመሆኑን ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የፖለቲካ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በአንድ ሉዓላዊ አገር ሁለት የተለያዩ ሕገ መንግሥቶች ኖረው እንደማያውቁና በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት መሠረት በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ሕገ መንግሥትን ማርቀቅ ውጤት አልባም ከመሆኑም በላይ በወንጀል ሕጉ "ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን የማፍረስ ወንጀል" እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ። ሰማያዊ ፓርቲ ከቡድን መብት ይልቅ ለግለሰቦች መብት የቆመ እንደሆነ ደጋግሞ ይደሰኩራል። ከብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነት ይልቅ የግዛት አንድነትን ማረጋገጥ ይኖርብናል በሚል ይከራከራል። በዚህ መሠረት የመሬት ባለቤትነትን ለግለሰቦች የሚሰጥ ሥርዓትን እመሰርታለሁ ብሎም ይናገራል።

እነዚህን ተግባራት መፈፀም ከፈለገ እነዚህን ለህዝብ አቅርቦ የህዝብን ይሁንታ በማግኘት ሊሆን ይገባው ነበር።
የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተወያይተውበት አገሪቱን ወደ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ለማራመድ እንደሚያግዝ ታምኖበት የፀደቀ እንደሆነ ይታወቃል።

ከፀደቀ በኋላም ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ተተግብሯል። የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ተረጋግጧል፣ የአገሪቱ ሠላም በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲገኝ አግዟል፣ ሁለንተናዊ ለውጥም ተመዝግቧል። ሕገ መንግሥቱ በሰጠው የመደራጀት መብትም ተጠቅሞ የተመሠረተው ሰማያዊ ፓርቲ ግን ሕገ መንግሥቱን ለመናድ ያስችለኛል ያለውን እንቅስቃሴ ሲያደርግ ይታያል።

በአገሪቱ ሕዳሴውን ለማረጋገጥ ከሚከናወኑት በርካታ የልማት ሥራዎች ጎን ለጎን መንግሥት ለዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር መጎልበት የበኩሉን ሚና እየተጫወተ ባለበት በአሁኑ ወቅት ኃይማኖትና ሌሎች አጀንዳዎችን ሽፋን በማድረግ የሚንቀሳቀሱ አካላት በአገሪቱ በፖለቲካው፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ እየተመዘገበ ያለውን ውጤት የመናድ ዓላማ አንግበው እየሰሩ ስለመሆናቸው ሳይታለም የተፈታ ነው።

ይህ ፓርቲ በአገሪቱ በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን በመከተል አጀንዳውን ከችግሮቹ ጋር በማቆራኘት በአገሪቱ ሁከትን ለመፍጠር እየሰራ ይገኛል። በሽብር ተግባር ተከሰው በአገሪቱ ሕግ ሥርዓት መሠረት በማረሚያ ቤት የሚገኙ ታራሚዎች ይፈቱ የሚል የሽብር መፈክር ይዞ በመውጣት ግለሰቦችን በመሣሪያነት ለመጠቀም የተለያዩ ጥረቶችን አድርጓል። አገሪቱ ሽብርተኝነትን ለመዋጋት እያደረገች ያለውን ጥረት ለማደናቀፍም የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉ ይነሳ በማለት ፓርቲው ቅስቀሳ አድርጓል። በዚህ ዙሪያ በሽብር ተግባራት ከተሰማሩ ቡድኖች ጋርም ትብብርን ፈጥሯል።

ኢትዮጵያ ከነበረችበት አስከፊ ድህነት ወጥታ በልማት ጎዳና መጓዝ ከጀመረች ዓመታት ተቆጥረዋል። መንግሥት የህዝቡን ኑሮ በመሠረታዊነት ለመቀየርና የአገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጠን  የሚያስችል የልማት ስትራቴጂ ነድፎ በመተግበር ድህነትን ታሪክ የማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። የልማት እንቅስቃሴው ከተስፋ ሰጪነት አልፎ የበርካታ ዜጎችን ህይወት በተጨባጭ መቀየር አስችሏል። በግብናው ዘርፍ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሚሊየነር አርሶ አደሮች ተፈጥረዋል። በከተማም በአነስተኛ ጥቃቅን ተነስተው ባለ ኢንዱስትሪ የሆኑ ዜጎች በርካቶች ናቸው። ይህንን የልማት ጉዞ ሙሉዕ ለማድረግና መላውን ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ደግሞ የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተነድፎ በጥሩ አፈጻጸም ላይ ይገኛል።

በዚህ ምክንያት የአገሪቱ መገለጫዋ ከነበረው የከፋ ድህነትና ሰቆቃ በመላቀቅ ቀጣይነት ያለውን ልማት በማረጋገጥ ላይ ትገኛለች።  የነበራት የረሃብና የሰቆቃ ገጽታ ተቀይሯል። በአሁኑ ወቅት  ፈጣን ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉ አገራት ተርታ መሰለፍ ችላለች። በአገሪቱ እየተመዘገበ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ ለማፋጠንና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድን ተግባራዊ ለማድረግ ርብርብ በመደረግ ላይ ይገኛል። አገሪቱ ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ለምታደርገው ጥረት መሠረት ይጥላል ተብሎ በሚገመተው ይህ እቅድ በርካታ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ተነድፈው በግንባታ ላይ ይገኛሉ።

ከእነዚህም መካከል የስኳር ፋብሪካዎች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች፣ የባቡር ሐዲድ፣ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ መንገዶችና ሌሎች በርካታ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው። አገሪቱ እነዚህን ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶችን በምትገነባበት ወቅት ግን የኢትዮጵያውያንን ብልጽግና የማይፈልጉ ወገኖች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ልማቱን ለማደናቀፍ ያለሙ የተለያዩ ሙከራዎች መቃጣታቸው አልቀረም።

አንዱ የአገሪቱን አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት መሠረት ይሆናል በሚል ታቅዶ እየተሰራበት ባለ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች ላይ ያነጣጥራል። ከእነዚህ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ደግሞ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ነው። በኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብና አቅም እየተገነባ የሚገኘው ይህ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ሲጠናቀቅ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል እንደሚያመነጭና ኢትዮጵያን ከጎረቤት አገራት ጋር በኢኮኖሚ እንደሚያስተሳስር ከማስተሳሰሩም በተጨማሪ አገሪቱ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያግዛል። በቅርቡ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት 40 በመቶ በላይ የሚሆነው የግድቡ የግንባታ ክንውን ተጠናቋል። ግድቡ ከኢትዮጵያ አልፎ የሱዳንና የግብጽን ህዝቦች ተጠቃሚ እንደሚያደርግም የዘርፉ ምሁራን ይተነትናሉ።

ይህንን የተገነዘቡ የኢትዮጵያ  ህዝብ ጠላቶች በዚህ ትልቅ ፕሮጀክት ዙሪያ የተለያዩ አፍራሽ እርምጃዎችን ከመውሰድ አልተቆጠቡም። ደረጃውን ላይጠብቅ ስለሚችል ቢደረመስ ግብጽንና ሱዳንን ለጎርፍ አደጋ ይዳርጋል፤ ግንባታው የግብጻዊያንን የውኃ መጠን እንዲቀንስ ያደርጋልና ሌሎችም አፍራሽ ሃሳቦች በማራመድ የኢትዮጵያ ህዝብ ልማትን ለማደናቀፍ ያለመ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በሌላ በኩልም ይህች አገር በዚህ መልክ እድገቷ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ መበልፀን አይቀሬ መሆኑን ያረጋገጡ ወገኖች እስካሁን በኢትዮጵያ ህዝብ ስም እየለመኑ ለግል ድሎትና ቅንጦት ያውሉት የነበረው የእርዳታ ምንጭ እንደሚደርቅ በመገንዘብ ልማቱን መቃወም ዓይነተኛ መፍትሄ አድርገው በመሥራት ላይ ይገኛሉ። አገሪቱ ከእርዳታ ሰጪዎችና ከምዕራባዊያን ፍላጎትና ጥገኝነት ሙሉ በሙሉ ትላቀቃለች የሚል ሥጋት በማሳደር እንቅስቃሴያቸውን በተለያየ መልክ እያደረጉ ይገኛሉ።

በተለይ ደግሞ ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ ግድቡ በኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ ገንዘብና እውቀት  የሚሰራ በመሆኑና ኢትዮጵያውያንን ለዘመናት ሲቆጩበት የነበሩት የአባይ ወንዝ ጥቅም ላይ በመዋሉ ከአንዳንድ ሆድ አምላካቸው የሆኑ ከሃዲዎች በስተቀር መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ አንድ መንፈስና ሃሳብ ያመጣ ስለሆነ ይህ አንድነት ለሌሎች ትላልቅ ልማቶች ተሞክሮ

ስለሚሆን የአገሪቱ የእድገት ጉዞ እውን መሆኑን የሚያመላክት ሆኖ ስለተገኘ የኢትዮጵያ ማደግና የህዝቦቿ መበልፀግ የሚያማቸው ቡድኖች ስልታቸውን እየቀያየሩ ልማቱን መቃወማቸውን ቀጥለውበታል።

ከዚህ የተነሳ የአገሪቱን የልማት ጉዞ ከተቻለ ለመቀልበስ ካልሆነ ደግሞ ለማደናቀፍና ለማጓተት  ያስችላል ያሉትን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ለዚሁ እኩይ ተግባራቸው የተከተሉት ስትራቴጂ በአገሪቱ በመካሄድ ላይ በሚገኙ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ዙሪያ መሠረት የለሽ ዘገባዎችን በማቅረብ ለዓለም ኅብረተሰብ እንዲሁም በተለያዩ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዛባ አመለካከት ይዘው ልማቱን እንዳይደግፉ ማድረግ፤ በአገር ውስጥ ላሉ ዜጎችም እርስ በርስ በመከፋፈል ለልማቱ የሚያደርጉትን ተሳትፎ እንዲቀዘቅዝ ለማድረግ ያለመታከት በተከታታይ ዘመቻ ከሚያደርጉ ተቋማት አንዱ ሂዩማን ራይትስ ዎች ነው።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ያለመታከት በተከታታይ መሠረት የለሽ ዘገባዎችን በመበተን የአገሪቱን ልማት ለማደናቀፍ እየሰራ ይገኛል። በቀደሙት ዓመታት በአገራችን በመገንባት ላይ ባለው በጊቤ ሦስት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ዘመቻ ከፍቶ መንቀሳቀሱ ይታወቃል። በኢትዮጵያና በኬንያ ህዝቦች መካከል መቃቃርን ለመፍጠርም ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል። የጊቤ ሦስት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ የቱርካና ሐይቅ ውኃ መጠንን እንዲቀንስ ያደርጋል፣ በቱርክና ሐይቅ ህይወታቸው የተመሠረተ የአካባቢው ህዝቦች አደጋ ላይ ይወድቃሉ የሚል ማደናገሪያ በተከታታይ ሲያቀርብ ቆይቷል።

ይህ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተብዬው ድርጅት የኢትዮጵያ ህዝብ በገዛ የራሱ የተፈጥሮ ሃብት እንዳይጠቀም ከኢትዮጵያ አልፎ የሚደርሳቸው ህዝቦች እንዳይጎዱ ፍላጎቱን በተለያየ መልክ እየገለፀ  ቢገኝም ከቱርክና ጋር ተያይዞ እያነሳው ያለው ጉዳይ በሁለቱም አገራት ህዝቦች ተቀባይነት ባለማግኘቱ የተነሳ ያለመው ግጭትን የመቀስቀስ ዓላማ አልተሳካለትም። ኢትዮጵያና ኬንያ ልማቱ ሁለቱንም አገራት የሚጠቅም መሆኑን በመገንዘብ ለጋራ ጥቅም ትብብራቸውን ቀጥለውበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከዚሁ ከጊቤ ንወጣ በኦሞ ኩራዝ ትኩረቱን በማነጣጠር በአካባቢው የሚኖሩ ብሄረሰቦች አኗኗር እንዳይቀየር የቱሪስት መስህብ ሆነው ኋላ ቀር አኗኗር እንዲኖሩ፤ ለማህበራዊ ሣይንስ ተመራማሪዎች ጥናት አመቺ ሆነው ባሉበት እንዲኖሩና በእነዚህ ህዝቦች ስም የሚነግዱ አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ገቢ እንዳይደርቅ በማሰብ የኦሞን ባህላዊ አኗኗር ወደ ዘመናዊነት መቀየር የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው በሚል ተከታታይ ዘመቻ አድርጓል። የህዝቡ በመንደር መሰባሰብ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ማግኘትና ከነበራቸው አኗኗር የተሻለ ህይወት መኖርን  የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው ሲል ለፍፏል።

ከዚህም አልፎ መንግሥት በአገሪቱ ህግና ሥርዓትን ለማስፈን የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በተደጋጋሚ በማውገዝ ረገድ ለሂዩማን ራይትስ ዎች አቻ አይገኝለትም። ድርጅቱ በዚሁ ዓመት መጀመሪያ ባወጣው ሪፖርት  ደግሞ የፖለቲካ እስረኞች ያላቸው ግለሰቦችን ማዕከል ያደረገ የተዛባ አስተያየት አቅርቧል።

በመግለጫው ያሰፈረው በአገሪቱ ባሉ ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ ታራሚዎች ላይ ተገቢ ያልሆነ ስቃይ ይፈፀምባቸዋል የሚል ቅጥፈት ነው፤ በመጀመሪያ በአገሪቱ የተለየ የፖለቲካ ሃሳብ በማራመዱ የታሰረ አንድም ዜጋ በሌለበት ሁኔታ የፖለቲካ እስረኞች ለስቃይ እየተዳረጉ ነው የሚል የፈጠራ ዘገባ ማውጣቱ እንደ ቀደሙት ሪፖርቶቹ ሁሉ የአገሪቱን ገጽታ ለማበላሸት አልሞ መነሳቱን ያሳያል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች ``የፖለቲካ እስረኞች `` እያለ የሚያንቆለጳጵሳቸው ግለሰቦች ወደ ማረሚያ ቤት የገቡት በወንጀል ድርጊታቸው መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ አስረግጦ ያውቀዋል። በአገሪቱ የፍርድ ሂደት መሠረት ጥፋታቸው ተረጋግጦ የታሰሩ ናቸው። የአንዳንዶቹ ጉዳይም በፍርድ ሂደት ላይ የሚገኝ ሆኖ እያለ የሂዩማን ራይትስ ውንጀላ ግን ግለሰቦቹን ለማገዝ ያነጣጠረ ሳይሆን የያዘውን የኢትዮጵያን ልማት የማደናቀፍ አጀንዳ ለማሳካት ያለመ ነው።

እነዚህ በወንጀል ድርጊት ተከሰው ለፍርድ የቀረቡ ግለሰቦችም ቢሆኑ መብታቸው ተጠብቆና አግባብ ያለው አያያዝ ተደርጎላቸው በመታረም ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው። ባለፉት ከአሥር ዓመታት በላይ በተከታታይ የወጡ የሂዩማን ራይትስ ዎች ዘገባዎች መሠረተ ቢስ መሆናቸው በየጊዜው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር መረዳት ይቻላል።

ድርጅቱ በኢትዮጵያውን ዘንድ መደናገርን ለመፍጠር እና የዓለም ኅብረተሰብን በማሳሳት የአገሪቱን በጎ ገጽታ ጥላሸት ለመቀባት አልሞ እየተንቀሳቀሰ ለመሆኑ ሪፖርቶቹን የመረመረና በአገሪቱ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ያየ ማንም ሰው ይመሰክራል። "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል" የሚለውን አባባል ተከትሎ ተደጋጋሚ የሐሰት ጋጋታ የሚለቀው ሂዩማን ራይትስ ዎች በመሠረቱ ከኢትዮጵያ መንግሥት በተሻለ መንገድ ለኢትዮጵያ ህዝብ ተቆርቋሪ ሆኖ ሳይሆን በሰብዓዊ መብት ስም ድብቅ አጀንዳውን ለማሳካት እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ድርጅት ለመሆኑ እስካሁን ይፋ ያደረጋቸው የተዛቡ መረጃዎች አብነት ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝብ በአገሪቱ ያለው የልማት እንቅስቃሴ ተጠቃሚ መሆኑን አረጋግጧል። ልማቱን የሚያፋጥንለት እንጂ የሚያጓትትና የሚያሰናክልን ማንኛውም አካል አይሻም።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የተለመደ ቅጥፈትም ውኃ የማይቋጥር በመሆኑ በህዝቡ ተቀባይነት የማያገኝ ተረት ተረት ሆኖ መቅረቱ እሙን ነው - የሐሰት ጋጋታ እውነትን ያደበዝዝ ይሆናል እንጂ ሊለወጥ አይችልምና። የኢትዮጵያን ልማት ለማደናቀፍ አነጣጥሮ የሚንቀሳቀሰው ሌላው ተቋም ደግሞ ኢንተርናሽናል ፍሪደም ኦፍ ኤክስቼንጅ ክሊሪንግ ሐውስ የተሰኘው ተቋም ነው። ተቋሙ በጎ አድራጎትን የሚመለከት መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል።

የዚህ ሁሉ መነሻው ግን እየተናገሩ ያሉት የሰብዓዊ መብት የመጣስና ያለመጣስ ጉዳይ ሳይሆን የቆሙለት ህቡዕ አጀንዳን የማሳካትና ያለማሳካት ጉዳይ ነው። እነዚህ ተቋማት ኢትዮጵያ ማደግ የለባትም ህዝቧም መበልፀግ አይኖርበትም የሚል

ድብቅ ዓላማ የያዙና የሰብዓዊ መብትን በሽፋንነት የሚጠቀሙ ተቋማት እንደሆኑ በብዙ አስረጂ ማየት ይቻላል።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የአሜሪካ የስለላ መረብ በተለያዩ አገራት የግል ህይወትና የእለት ተለት እንቅስቃሴ ጣልቃ ገብቶ እየሰለለና የግል ስልካቸውን እየጠለፈ ለሚያደርገው የሰብዓዊ መብት ጥሰት ያነሳው ነገር የለም። የጀርመን መራሔ መንግሥት አንጌላ መርክል የዚሁ ችግር ጠለፋ ሰለባ መሆናቸው ይታወቃል።